## ክፍል ሁለት

## አማሬ ለምን እና በማን?

kidusl@yahoo.com

የዛሬ ሶስት አመት የሞሀ ለስላሳ መጠጦችን አለመጠቀም አድማ ተጠርቶ ፤ አድማውም በኢትዮጵያ ህዝብ ተቀባይነት አግኝቶ ፤ ሞሀ ደንበኛ አጥቶ ሲንገዳገድ ከዲያስፖራው ትልቁን ለቅሶ ሲያለቅስ የነበረው የኢትዮጵያ ፈርስት ድህረገጽ ባለቤት ቤን ነው:: ቤንም ከኢትዮጵያውያን ለለቅሶው መህረብ ሳይሆን ምላሽ ሲሰጠው «እወስደዋለሁ» ሲለን የነበረው እርምጃ ዌብሳይቱን መዝጋት ነበር:: በወቅቱ በኦዲዮ ባስተላለፈው መልእክቱ እሱ ድህረገጽ ላይ የተለያየ ጽሁፎች ያላቸው ሰዎች ጽሁፎቻቸውን እንዲሰበስቡ ከገለጸ በኃላ ፤ ለምን ዌብሳይቱን ለመዝጋት እንዳሰበ ተንትኖልን «እንዴት ሼህ አላሙዲ ይነካሉ?» የሚል ተግሳጹን አቀረበልን:: ድህረገጹ ከዛሬ ነገ ተዘጋ ሲባል ይኸው ሶስት አመቱ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል:: ሀሳቤን ያስቀየረኝ ከእድምተኞቼ ድህረ-ገጹን እንዳልዘጋው ያገኘሁት ከፍተኛ ድጋፍ ነው ብሎናልም:: ቤን ከሼህ አላሙዲ ድጋፍ እንደሚደረግለት ሲነገር የነበረው እውነታነት እንዳለው ወይም እንደሌለው እሱ ይወቀው-«ህሊና እና ሙያዊ ስነ-ምግባር» አለኝ ስለሚል:: ስዩም መስፍንን-በረከት ስምኦንን-አባዱላ ገመዳን-አዜብ መስፍንን-ሙሼ ሰሙን እና ወዘተ ኢህአዴጎችን.. ደግሞ ደጋግሞ ቃለ-መጠይቅ የማድረግ ብቸኛ መብት ያለው ኢትዮጵያዊ ቢኖር ቤን ዘ አላሙዲፈርስት ነው:: ዋልታ እና አይጋፎረም የቤንን ያህል ቃለ-መጠይቅ ለኢህአዴጎች አላቀረቡም:: እስካሁን ቤን ቃለ-መጠይቅ ያልሰጠው ብቸኛ ባለስልጣን ጠ/ሚ/ር መለስ ነው::

ወደ አማሬ ጉዳይ ስንመጣ መጀመሪያ በሚድሮክ ዝርክርክነት ላይ ሪፖርተር ዘገባ ሲያወጣ እንደተለመደው «እንዴት አላሙዲ ይነካሉ!» ብሎ ወገቡን ይዞ የተከራከረው የ«ኣላሙዲፈርስት» ድህረ-ገጽ አዘጋጅ ቤን ነው:: በኢዲቶሪያሉ ላይ ለመወረፍ በሚደረግ ዲፕሎማቲካዊ ዘይቤ ሪፖርተርን አሞግሶ «አላሙዲን አትናገር!» የሚለውን የተለመደውን ዛቻ አቀረበ (http://www.ethiopiafirst.com/news1.html):: ደርባ ሲሚንቶ ፋብሪካ 1.5ቢሊዮን ብር የፕሮጀክት ማስፋፍያ እቅድ እንዳለው ሲገልጽ በተመሳሳይ መልኩ ራሱ ደርባ 16ሚሊዮን ብር ጂቡቲ ላይ እየከሰረ እንደሆነ የሚገልጸው የሪፖርተር ዜና ምነው ቤን ሳያቀርበው ቀረ? ወይስ የደርባ ማናጀር ሐይሌ አሰግዴን (የቀድሞው የመለስ ካቢኔ አባል) ማስቀየም አልፈለገም? እርግጥ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የሼኩ ኪሳራ የአገሬን ኪሳራ ያህል አያንገበግበኝም:: የሚያንገበግበኝ ለሼኩ ብቻ ከአገር ውጪ ሲሚንቶ ማምጣት መፈቀዱ ነው::

አማሬ ላይ በቤን የተጀመረው የቃላት ጥቃት ቤን ላይ አላበቃም:: የሳምሶን ማሞው «ኢትዮ ቻናል» ተከታታይ እና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ጽሁፍ በጸሀፊ ገ/ጻዲቅ ህሉፍ ስም ይቀርብ ጀመር:: (አንባብያን ለምን ይህ «ገ/ጻድቅ ህሉፍ) የብእር ስም እንደተመረጠ ስሙን እና ትርጉሙን ገምቱ):: የ«ኢትዮ-ቻነል» አምደኛ እና «ደባ አመንሲሳ» የተባሉት ጸሀፊዎች ጽሁፋቸው ስካን እየተደረገ አላሙዲፈርስት ድህረገጽ ላይ የአንበሳ ድርሻቸውን አገኙ:: ቤን ለብቻው ሳይሆን ጨንቱን ከሚጮሁለት ጋር አብሮ ለአማሬ እና ሪፖርተር አርፋችሁ ተቀመጡ ማለታቸውን ቀጠሉ::

«ኢትዮ-ቻነል» ጋዜጣ ከአመት በፊት ገበያ ላይ መዋል እንደጀመረች የኢትዮጵያ ህዝብ ከጋዜጣው ጀርባ ማን እንዳለ አልጠፋውም:: የሚሚ ስብሃቱን ባልተቤት መተካት የፈለገው የቀድሞው የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጋዜጠኛ ሳምሶን ማሞ በአዲስ መልኩ «የግል ጋዜጣ» ይዞልን ብቅ አለ:: እቺ የሳምሶን ማሞ «አብዮታዊ ዲሞክራሲ» ጋዜጣ መሆንዋ ሲነቃ ፤ ሳምሶን ጋዜጣዋ ከማንም ያልወገነች «ውሸትን የምትፈራ» «የግል» ጋዜጣ

እንደሆነች በራስዋ በጋዜጣዋ ላይ ሊነግረን ይሞክር ነበር፡፡ ጋዜጣዋ ግን የምትፈራው ውሸትን ወይስ ውሸታምን?

ኢትዮ-ቻነል ከምርጫው በኃላ የነጻ ፕሬሱን ሊመስሉ ከሞከሩ ጋዜጦች አንድዋ ነች፡፡ ይዘትዋ ፤ ዜናዋ እና አቀራረብዋ ምን እንደምተሸት ለማወቅ አንዱን እትም ከአዲስ አበባ አስመጥታችሁ አንብቡ፡፡ሳምሶን ማሞ የጋዜጣዋን ቢሮ ከሜጋ ህንጻ (ከቀዳማይቷ እመቤት ቢሮ ፊት-ለፊት) እስከ 10ሺኅ ብር በሚገመት የወር ኪራይ በተከራየው ቪላ ላይ ነው ያደረገው፡፡ ቦሌ መስመር በተለይ ፒኮክ አካባቢ (የድሮው ገና ባር ወይም የአሁኑ ሲቲ ፕላዛ (ሲቲ ካፌ) አካባቢ) የግል ጋዜጣ ድርጅት ቢሮ አይደለም ግዙፍ አገር በቀል ድርጅት ቪላ ለመከራየት አቅሙ ከየት እንደሚመጣ እንገምት፡፡

ወደ ቤን ስንመጣ የአማረን አደጋ ሲሰማ ሪፖርተር ቢሮ ደውሎ «ሲንየር» ጋዜጠኛ አነጋግሮ አማረ ደህና መሆኑን ሊያበስረን ወንጀለኞቹን ደግሞ ሊያወግዝ ሞከረ፡፡ በነገራችን ላይ የቀደመው ወንጀለኛ ማን ነው?ወንጀሉን የፈጸመ ወይስ ወንጀሉ እንደሚፈጸም የሚያውቅ ወይም የተናገረ?

አማረ አረጋዊ ከትጥቅ ትግሉ በኃላ በተለያየ ምክንያት ህይወታቸው ካለፈው ከክንፈ እና ሐየሎም ለየት ባለ መልኩ እና ሊሞት በማይችል መልኩ ሊቆስል የበቃው እንዲሁም በጠራራ ጸሀይ እና ህዝብ በተሰበሰበበት ጥቃት የተፈጸመበት ሊገደል ታስቦ ነው የሚለውን ይበልጥ አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡ አማረን ለመግደል ከዚህ የተሻለ አማራጮች ጠፍቶ አይደለም፡፡ አማረን ለመግደል ተሞከረ ከሚባል ለማስጠንቀቅ ተሞከረ ብንል ይቀላል፡፡ ከዚህ በፊት ጎንደር ድረስ የታሰረው አሁን ደግሞም በጦረኛ ቃላቶች ተጀምሮ በጦረኛ መሳሪያዎች የቆሰለው «አርፈህ ተቀመጥ» ለማለት ነው፡፡

## <u>የጽሁፉ አላማ</u>

ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚያስማማ አንድ ጉዳይ ቢኖር የኢህአዴግ መበስበስ እና አገርን የመምራት ብቃት እንደሌለው ነው፡፡ የፖለቲካ ድክመት ፤ በህዝብ ተቀባይነት ማጣት ፤ የሙስናው መንሰራፋት እና የሙስናው ግዝፈት የኢህአዴግ መለያዎች ናቸው፡፡

ኢህአዴግን ከስልጣን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ውስጥ ያሉት ሀይሎች ሁለት እንደሆኑ ይታወቃል፡፡

አንደኛው ጠላት ኢህአዴግ ብለን የምንጠራው ሀገሪትዋን የሚመራው፤ የፖለቲካ ስልጣን ያለው የኢህአዴግ የፊት ገጽታ ነው፡፡

ሁለተኛው ጠላት በኢህአዴግ ከፍተኛ ተጠቃሚ የሆነው፤ የኢህአዴግ የፖለቲካ ኪሳራን የሚፈልግ ፤ የኢህአዴግ የቁጥጥር ድክመት የሚጠቀመው «ባለሀብቱ ኢህአዴግ» ነው፡፡ ባለሀብቱ ኢህአዴግ ስንል አላሙዲን ማለታችን አይደለም፡፡ አላሙዲ አንደኛው ጠላት ላይ የሚፈረጅ የኢህአዴግ የፊት ገጽታ ነው፡፡ «ባለሀብቱ ኢህአዴግ» ማለት እንደነ የምሩ ነጋ «ደንበል ሲቲ ሴንተር» አይነቱ በባንክ እዳ ህንጻቸው በሀራጅ እንዲሸጥ በባለሙያዎች ታዞ ትእዛዙ በፖለቲካ ትእዛዝ ተሸሮ ፤ አዲስ የመንገድ ኮንትራት ተሰጥቶአቸው እዳቸውን እንዲከፍሉ ስለሚደረጉት ድብቅ ግን እልፍ ጠላቶች ነው፡፡

## <u>ለምን ኢህአዴግ አይወድቅም?</u>

ይቀጥላል